# በጋምቤላ በኩል በህገወጥ መንገድ የገባ 50 ክላሽንኮቭ መሳሪያ ደብረ ብርሃን ላይ በቁጥጥር ስር ዋለ

November 20, 2018




አዲስ አበባ፣ ህዳር 11፣ 2011 (ኤፍ.ቢ.ሲ) በጋምቤላ በኩል የገባ 50 ክላሽንኮቭ፣ አንድ ላውንቸር እና 40 ካርታ ጥይት በቁጥጥር ስር ዋለ።

የጦር መሳሪያው በብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከጋምቤላ ጀምሮ ክትትል ሲደረግበት ቆይቶ አዲስ አበባን አልፎ ደብረ ብርሃን ላይ ነው የተያዘው።

ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የደረሰው መረጃ እንደሚጠቁመው በቁጥጥር ስር ከዋሉት 50 ክላሽንኮቭ ውስጥ 37ቱ ባለሰደፍ ሲሆኑ፥ ቀሪዎቹ ታጣፊ ናቸው።

የጦር መሳሪያው በገልባጭ መኪና የብረት ረብራብ ተሰርቶለት በመጓጓዝ ላይ እንዳለም ነው የተያዘው።